# ጣኦት ጠራቢው ያሬድ ጥበቡ

የሴፍ ከዋሺንግተን ዲሲ

አቶ ጥበቡ **ታሪክ ራሱን ይደግማል** የሚል ባለ ሁለት ገጽ ጽሁፍ በፌስ ቡካቸው ለጥፎት አነበብኩት። ሁለት ገጽ ቢሆንም የተጻፉት ዝባዝኬዎች የመጽሃፍ አቅም ይወጣዋል። ከጽሁፉ አንዲት ጠቃሚ ሃቅ ማውጣት ቢሳነኝም ግምኛ የሆነውን መልዕክታቸውን ግን ቆጥሮ መጨረስ አቅቶኛል። ለምን ሰው እንዲህ ይጃጃላል ብዬ ጽሁፍን ወድ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ወርውዬ ነበር። ግን የበርካታ የዋሆችን አዕምሮ ያቆሽሻል በማለት የጽሁፍን ከፋትና ተንኮላዊ ተልዕኮ ማጋለጥ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ። በከንቱ ሰዓቴን ባጠፋም ባላጠፋ።

እንዲህ ይላል ጸሐፊው " ሳንታጠቅ **ሱሪያችንን ዝቅ** እንዳደረግን የኢትዮጵያ ህዝብ ሲያጋልጠን ይህ የመጀመሪያችን አይደለም። በእኔ እድሜ እንኳ **ሶስተኛው** መሆኑ ነው። **የ1966ቱ የይካቲት አብዮት፣ የ1997 ምርጫና** ይህ የዘንድሮው **20085 እስከ 2009 የህዝባዊ እምቢተኝነት።**" በመጀመሪያ ደረጃ ጣኦት ጠራቢው ሱሪያችንን ዝቅ እንዳደረግን የምትለዋ ሃረግ በስፋት ስታይ ሴቶችን ያገለለ አባባል መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም። ጠንካራ ቃል ይመረጥ ከተባለ ደግሞ ጠራቢው ትምክህተኛ ስለመሆኑ ጠቋሚ ሃረግ ነው። ባለመዘጋጀታችን ሕዝቡ ሶስት ጊዜ እንደታዘባቸው ይናገራል። ካጀማመሩ የመሰለኝ ሕዝቡ በትግሉ ያመጣውን የየካቲቱን አብዮት በደርግ ስለመቀማ፣ ደርግን ያንበረከከው ሕዝባዊ አመጽ በወያኔዎች ስለመሰለቡ ነበር። ስለ ደርግ አወዳደቅና ስለ ወያኔ የሕዝቡን አብዮት መቀማት ያሬድ ሊያወራልን አይፈልግም። ምክንያት አለው። የገረመኝ ነገር ደግሞ የየካቲትን አብዮት ከምርጫ ውድድሮጭ ጋር ለማወዳደ መቃታቱ ነው። እነ ያሬድ ከኢሕአፓ ከድተው ኢሕአዴግ ስር ተለጥፈው ከፍተኛ ሴራ በኢትዮጵያ ላይ አካሄደዋል። ጣኦት ጠራቢው ይህን የከረፋ ታሪኩን ይነግረናል ብዬም አልሞኝም። ግን የ97ቱ ሆነ በተከታታይ የተካሄዱት ምርጫዎች የከሸፉት መሪ አጥተው አልነበረም ያሬድ ሊነግረን እንደሚሞክረው።

የጣኦት ጠራቢው አንዱን ካንዱ የማወዳደር ዘዴው የሚጠርበውን ታቦት ከፍ ከፍ ለማድረግ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ በልዝብ ሴጣናዊነት የሕዝብ ወገን የሆነውን ድርጅት ለማጣጣል ነው። እንኳን ይህችን መናኛ ተንኮል ቀርቶ የዝብ ጠንጋራም እናውቃለንና ድካሙ ምርት የለውም። እንዲህ ይላል ጣኦት ጠራቢው ". . . **<u>የኢህኢፓ እርሾ</u> የሆነው ሃይል በፍልስጤምና በ<u>ኤርትራ</u> ስልጠና ላይ እያለ የየካቲት አብዮት ከተፍ ይላል** . . . " ይህች ስንኝ ትንሽ ብትሆንም የያዘችው ማደናገሪያና ማሳሳቻ ቀላል አይደለም። ሁለት አይን ያወጡ ውዥንብሮችን ሆን ተብሎ ተሰንዝሯል። አንደኛ የኢሕአፓ እርሾ ሳይሆን የኢሕአሰ እርሻ ነው ዕውነቱ። <u>ኢህአሰ</u> ማለት <u>ኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት</u> ሲሆን ኢሕአፓ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ማለት ነው ምናልባት ያሬድ ተረስቶት ከሆነ። ይህ ሰራዊት ደግሞ የኢሕአፓ ሰራዊት ነበረ። እርሾው በኤርትራ ስልጠና አልተሰጠውም፣ ሰልጥኖ የመጣው ከፓላስቴይን ነው። የዚህ አባባል ዳር ዳሩ ኢሕአፓ ከኤርትራ ነጻ አውጭዎች ጋር የተወጅጀ ነበር ለማሰኘት ነው። በኢሕአፓ ውስጥ ያለፈ ሰው በኢህ አሰና በኢሕአፓ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት አያውቅም ለማለት ይከብዳል። ብሎም ደግሞ ለኤርትራ ነጻነት ይታገሉ የነበረ ድርጅት እንኳን የኢሕአሰን እርሾ ሊያሰለጥን ቀርቶ ድራሹ ሊያጠፋው ከወያኔ ጋር አብረው እንደወጉት ማስታወሱ ለታቦት ጠራቢው የሚሳነው አይደለም።

ታቦት ጠራቢው ያሬድ ጥበቡ የነበረበትን ግን ከድቶት ወደ ወያኔ ጉያ የገባው በጽናት የዘለቀውን ኢሕአፓን በመጥፎ ዓይን ቢያየው ለምን ብለን አንከራከርም። ከሕዝብ የማያቀራርበው ሙብቱ ነው። ኢሕአፓን ለማሳነስና እንዲያውም የለም ለማለት የፈለገው በክፋት "ጥበቡ" ነው። " **ሰራዊቱ የካቲት 23 ቀን አሲምባ ላይ የትጥቅ ትግል መጀመሩን ሲያበስር ከሁለት ቀን በኋላ ታሪካዊው የመሬት ላራሹ ታወጀ። <u>በአዋጁ ተራማጅነትና ስርነቀል ባህሪው</u> የተነሳ ከሳምንት በኋላ የኢህአሰ ሰራዊት ውስጥ " <u>የመሬት አብዮት ተጠናቋል እኛ እዚህ ምን እናደርጋለን?</u>' የሚል ጥያቄ ተነስቶ <u>ለሁለት ተከፈለ። ግማሹ አዲግራት የሚገኘው የደርግ ጦር ጋር ገብቶ እጁን ሰጠ።</u>"** በማለት ይጽፋል። ደርግ በሕዝቡና በተራማጁ ኢሕአፓ ግፊት ሳይወድ የመሬ አዋጅ አድርጓል። ችግሩ ግን አዋጁ <u>በምንም መስፈርት ተራማጅና ስርነቀል አልነበር</u>። አዋጁ መሬትን የመንግስት

እንጅ የግለሰብ አላደረገውም። ሕዝቡ ደግሞ መሬቱ የራሱ እንዲሆን እንጅ ለመንግስት መፈንጫ እንዲሆን አልነበረም የታገለው። ለዚህም እኮ ነው ዛሬ የመሬት ጥያቄ መልስ አላገኘም የሚባለው። ኢሕአፓ ሕዝባዊ ትግሉን የሚያካሄደው ከሕዝብ መብቶች አንዱ ለሆነው ለመሬት ጥያቄ ብቻ አልነበረም፣ አይደለምም። ሕዝባዊ መንግስት መመስረት አለበት፣ የሰብዓዊና የዲሞክራሲ መብቶች መከበር አለበት፣ ፍትህ መሟላት አለበት. . . ወዘተ። እነዚህንና መሰል ሕዝባዊ ፍላጎቶች ሳይሟሉ ትግሉ መቆም አልነበረበትም። ሰራዊቱ ለሁለት መከፈሉን በደስታ ያበሰርና አንዱ ክፍል እጁን ለደርግ ሰራዊት ሰጠ ብሎ ስለ ግማሹ የት እንደገቡ ሳይነግረን ለመሸወድ ሞከረ። አንተ ለማለት ባትወድም እኔ ልርዳህ። ያልተናገከለት ግማሹ ከነሱ ውስጥ አንተን ጨምሮ ወደ ወያኔ ተቀላቀላችሁ። ታሪክ ነውና የታሪክን ሃቅ በሚገማ ማኖር ይጠበቅብሃል። ኢሕአፓን ጠልተው ወደ ደርግ ገቡ ብለህ በድፍረት የተናገርከውን ያህል እኛ ደግሞ ኢሕአፓን ጠልተን ወደ "ተራማጁ" ወያኔ ገባን ለማለት ወኔ አጣህ። ባንተ ቤት የሰራዊቱ መበተን የድርጅቱ መበተን ነው ብለህ ለማቀረብ ነው እየደከምክ ያለኸው ጣኦት ጠራቢው።

ያሬድ ጥበቡን ጣኦት ጠራቢ ያልኩት ያለምክንያት አይደለም። ለነገሩ ይህን ጣኦት ጠራቢ የሚለውን ቃል የተዋስኩት ከኢያሱ አለማየሁ ነው። ጣኦት ጠራቢዎች የመለያ ባሕሪ አላቸው። ትኩረታቸው ከሕዝብ ይልቅ ግለሰብን አጎዝፎ ለማውጣት ነው ማለትም የግለሰብ ተክለ ስውነትን ለመስራት ነው። በራሳቸው አነሳሳሽነት ወይም ብላችሁ ጻፉ ወይም ተናገሩም ሊባሉም ይችላሉ። ከሚያጎዝፉት ግለሰብ ስም ፊት ታላላቅ ቅጽሎችን ወይም ቃሎችን ያስቀምጣሉ። ግለሰቡን/ግለሰቧን ልዩ ፍጡር አድርገው ያቀቧቸውል። እንዲህ ይላል ጣኦት ጠራቢው ያሬድ፡-

**".. ያ ደፋሩና አርቆ አሳቢው የፓለቲካ ሰው ብርሃነመስቀል ረዳ** . . . " ሰውየው አርቆ አሳቢ ቢሆን ድርጅቱን ኢሕ እፓ በመከዳት ጸረ ኢሕ አፓ ስራዎችን ባልሰራ ነበር። ደፋር ቢሆን ኑሮ ልዩነቱን ድርጅቱ ውስጥ በመሆን የዲሞክራሲ መብቱን ተጠቅሞ መከራከር በቻለ ነበር። አልደፈረም አርቆም አላሰበም ነው ለያሬድ የምለው።

". . .**ዶክተር ብርሃኑ ነጋ . . . የሞቀ ትዳራቸውን፣ ኮሌጅ ያልጨረሱ ልጆቻቸውን፣ የሚያስጎመዥ ስራቸውን ትተው** . . ." ይህችኛዋ ደግሞ አስቂኝ ናት። ስንት የሕዝብ ወገን ታጋይ ነው የሞቀ ትዳሩን፣ የልጆቹን ቁምነገር ሳያይ፣ ማስጎምዥቱ እንኳን ይቅርና ቤተ ሰቡን የሚያስተዳድርበት ስራውን ትቶ ለትግል የቆመው፣ የተሰዋው። እንዲያው ከደሃው የዶክተሩ ሕይወት የተለየ ክብር ማግኘት አለበት? ጣኦት ጠራቢው የሚያቅለሸልሽ ስህተት ሰርተሃል።

" **ከትምህርቱም ሆነ ከስልጠናው በተነሳ ሰላማዊ ሕዝባዊ እምቢተኝነተኝነቱን እንደ ስነጥበበ የተካነውና ደረጃ በደረጃ አመራር በመስጠት ዛሬ ላለበት ብስለት ያደረሰን የጃዋር መሃመድ አስተዋጽዖ** . . ." ጀዋር መሃመድ ከነበረው ዘረኛ አመለካከት ተላቆ ኢትዮጵያዊ ከሆነ እኔም እደግፈዋለሁ። ለነገሩ ሕዝባዊ እንቢተኝነትን ለዘመናት ሲያስተምር የነበረውና አሁን በማስተማር ላይ ያለው ኢሕአፓ ስለመሆኑ ወደ ፍኖተ ዲሞክራሲ ራዲዎ ስርጭት ፋይል ገብተው ይፈትሹ። " "... ሳንዘጋጅ ከተፍ ያለብን የሕዝብ እምቢተኝነት . . . " ብሎ በጽሁፉ መግቢያ ላይ አስቀምጧል። "እንደ ጅዋር" ያለ ደረጃ በደረጃ አመራር እየሰጠ ያለ መሪ እያለ (ከት ብዬ ብስቅ ይፈረድብኛል?)

" . . **አብሪ ኮከባችን ብርቱኳን ሚደቅሳ** . . ." አርፋ የተቀመጠችውን ለምን ትነካካታለህ? ለነገሩ አብሪ ኮከብ ቃሉን ባልወደውም ' ሳንታጠቅ ሱራችንን ዝቅ እንዳደረግን . . " ከምትላቸው የሷ አስተውጽዖ ይጎላብኛል።

ሌላው የገረማኝ ነገር <u>ቢሆን ኑሮ የፓለቲካ ጨዋታ ነው</u>። " **ምናልባት የመኢሶንም ሆነ የኢሕአፓ መሪዎች የካቲት እንደተፈጠር ወደ ሃገራቸው ተመልሰው የነበራቸውን ስምና ዝና ተጠቅመው በመንገዳገድ ላይ ለነበረው የቀዳማዊ ሃይለስላሴ ስርዓት አማራጭ አሳይተው ቢሆን ኑሮ የወታደሮቹን ወደ ስልጣን መምጣት ያግድ ይሆን ነበር ብዬ ማሰላሰል እወዳለሁ።"** መልሱ ላንተ ተደብቆብሃል። እኔ ይሆን የነበረውን ልንገርህ። አንተ የምታሳንሰው ኢሕአፓ እኮ አገር ውስጥ ነበር ያኔ። ጨረቃ ላይ አልነበረም። ድርጅቶቹ ንጉሱ ፊት ቀርበው ቢሆን ኑሮ ኑሯቸው ከርቸሌ ይሆን ነበር። ቤንዚን ይዞ ወደ እሳት መጠጋት ማለት ነው። ". . . **ብርሃነመስቀል ረዳ በአፋር በረሃ አቃርጦ አሲምባ ለመግባት ካደረገው ተጋድሎ ይልቅ የየካቲት አብዮት ከተፍ ማለቱን ሲያውቅ ከኤርትራ ጓዙን ጠቅልሎ አዲስ አበባ ገብቶ ቁራጥ አመራሩን ሰጥቶ ቢሆን**

**ኑሮ ሃላ የተከሰቱት ችግሮች ይከሰቱ ነበርን? መቼም የማንመልሰው ጥያቄ ይመስለናል። ከዚያ ልምድ ግን ልንማርበት እንችላለን**." በራሱ ጥያቄ ራሱ ይመረቅናል" መቼም አውቆ ለማደናቆርና ለማደናገር መነሳቱን ማወቁ እንዳንሸወድ ይረዳናል። በመጀመሪያ የኢሕአሰ እርሾ ኤርትራ ውስጥ በፍላጎቱ አልነበረም የቆየው። ታግቶ እንኮ ነው። ታውቀዋለሃ ታሪኩን አውቀህ ለማወናበድ እንደሆነም አውቀንብሃል። እርሾው በኤርትራ በርሃ ታግቶ እያለ ኢሕአፓ ግን ከሕዝቡ ጎን ተሰልፎ ትግሉን በማፋፋም ላይ ነበር። ለራሱ ጥያቄ መልስ የለውም ይለንና ከዚህ ልምድ ግን ልንማርበት እንችላለን በማለት ካልተደረገ ሁኔታ ምን ልምድ መቅሰም እንደሚቻል ሊገባኝ አልቻለም።

ዛሬ ደግሞ አዲስ ተክለሰውነት በመጥረብ ላይ ነህ። " . . . **በአሁኑ ወቅት የብርሃኑ መገኛ ኤርትራ መሆን ያለበት አይመስለኝም። ከኤርትራ ይልቅ ዋሺንግተን ቢመጣ የኦሮሞና የአማራ ትግሎችን ለማስተባበርም . . . ብሎም ከምዕራባዊያን ጋር አስፈላጊ የሆነ የመተማመን ሁኔታ ላማማቻቸት . . . የብርሃኑ አመራርና ሰብእና አስፈላጊ መስሎ ይታየኛል . . .**" የኦሮሞና የአማራው ትግል በራሳቸው መሪዎች ብርሃኑ ይምራቸው ማለቱ ትዕቢት አይደለም ዕትጠራቢው? ከትዕቢትም አቅለሽላሽ ትዕቢት። አሁን ደግሞ ጃዋርን አውርደህ ጌታ ብርሃኑን አወጣኸው። አንድ ቦታ ላይ ደግሞ እንዲህ አልከን " . . . **ለሽግግር መድረክ አማራው ማስፈለጉ አከራካሪ አይደለም። አንድ ሶስተኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያካተተ ነው። እንደ ብርሃኑ የምጠራው ስም አላገኘሁም። . . . አዲሱ ለገሰ በእርጅና ራሱን ያገለለ ሰው መሆኑን ባውቅም ለእንዲህ አይነት የሽግግር መድረክ የሚረዳ ጨዋ ሰው ይመስለኛል።** ያንተ ብርሃኑ ነጋ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራን ሲባረሩ የወያኔን ውሳኔ ደግፎ የተባረሩትን ምሁራን እንደመደገፍ ቦታውን ለመሙላት የሄደ ሰው መሆኑን አታውቅም። ለቅንጅት መፍረስ ብቸኛው ባይሆንም ተቀዳሚ ሚና የተጫወተ ሰው ነው። የኢትዮጵያ ጠላት ከሆነው ሻቢያ ጋር የሚዶልት ነው። ለነገሩ የሻቢያና የወያኔ ጸብ ጊዜያዊ እንጅ ፍጹም አይደለም። ሻቢያ ከብርሃኑ ወያኔን ለጭንቅ ቀኑ ይፈልገዋል፣ ወያኔም እንዲሁ። በአማራው ድርጅት ውስጥ ከብርሃኑ እጅግ በጣም የሚሻሉ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን ታቦት ጠራቢው አትጠራጠር። ሰው ጥራ ቢሉህ ጋደኛህን አዲሱ ለገሰን ጠራሕ? ያም ሳይበቃህ ወያኔዎቹን ጄኔራል ጻድቃንና አቶ ገብሩ አይነቶቹም ለሽግግሩ ይጠቅማሉ ማለት ገባህ? ታሳዝናለህ አሳ ዝነህም ታሳፍራለህ።

የታቦት ጠራቢው ያሬድ ጥበቡ ተክለሰውነት ልዩ መሪዎች፡ ጀዋር መሃመድ፣ አዲሱ ለገሰ፣ ጄኒራል ጻድቃን፣ አቶ ገብሩ፣ ዶክተር ዲማ፣ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ። መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ። አንድ ያላልኩት ግን ራሱ ታቦት ጠራቢው ራሱን ከነዚህ "ሊህቃን" ውስጥ መመደቡን አንዘንጋ። " ሳንታጠቅ **ሱሪያችንን ዝቅ እንዳደረግን** የኢትዮጵያ ህዝብ ሲያጋልጠን ይህ የመጀመሪያችን አይደለም። የሚለው ራሱን ጨምሮ ነው። ይልቅ ሱሪህን ታጠቅ። ሕዝባዊ ትግሉ ካንተና ከጠረብካቸው ጣኦቶች ውጭ ስራውን እየሰራ ነው። ብርሃኑ ገለመሌ ክምትል የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ በሕዝቡ ቆራጥ ተሳትፎ ድሉሉን ይቀዳጃል። ሕዝቡ ማሸነፉ አይቀሬ ነው። የሕዝብ አመጽ ለጣኦቶችም ለጠራቢያቸውም ቦታ የለውም።